# ማን ይበጥስለት?

ብዙዎች ቢኖሩም ፣ አንቱ የተባሉ ፣ የማስታውሳቸው
በተግባር በስራ ፣ ከሁሉም አብልጬ ፣ የምኮራባቸው
የእድራችን ዳኛ ፣ ስለ አቶ ፈይሳ ፣ ላውራ ሰለሳቸው
ዛሬ ለዞረበት ፣ ለሚቀባዠረው ፣ እብድ ልጅ ላላቸው ።

የሰፈር አዛውንት ፣ የነ ጉደታ አባት ፣ ቆፍጣናው ፈይሳ
አርበኝነታቸው ፣ ያገራቸው ፍቅር ፣ መቼም አይረሳ
ትዝ ይሉኛል ዛሬም ፣ ስለሳቸው ታሪክ ፣ ማንነት ሳወሳ
አፈር ይቅለላቸው ፣ በጎ ምግባራቸው ፣ አያልቅም ቢወሳ
ግና ምን ያደርጋል ፣ ወይራ ዶግን ወልዶ ፣ ጀግና አባት ተረሳ
ምን ይሉ እኛ ፋኖ ፣ ልጃቸው ጉደታ ፣ ባገር ላይ ሲነሳ ።

ስንት ፈይሳዎች ፣ ደማቸው ፈሶላት ፤ ያቆዩአትን አገር
ልጃቸው ተነስቶ ፣ ያባቱን ደም እረግጦ ፣ ሊበትን በመንደር
ልሽንሽን ይለናል ፣ ካባት ያልቆየውን ፣ በጎጥና መንደር
ማንነቱን ክዶ ፣ አገሩን ሲያወግዝ ፣ አገርን ሲያስደፈር
ያባት ተግባር ጠፍቶ ፣ ልጅ ያበላሸው ወይ ፣ ሲጫናቸው አፈር ?

ነገር ተምታቶበት ፣ በከፋፍሎ ገዢ ፣ መርዘኛ ፈረንጅ
አጉል ስካር ሰክሮ ፣ አርባ አመት በሙሉ ፣ ታጥቆ የዘር ፈንጂ
ካባት ያልወረሰው ፣ በነጮች ተሰልቦ ፣ ወገኑን ሊፈጅ
ጥላቻን ሰንቆ ፣ ደም ሊያፈስ አድብቶ ፣ ጦርነት ሊያውጅ
አጥፍቶ ሊጠፋ ፣ የስመ ጥሩው ልጅ ፣ ሆኗል አገር ከጂ ።

ፈረንጅ ሆነ እንዳልል ፣ እንደኔው ጥቁር ነው ፣ ያውም ከአፍሪካ
አብረን የተማርን ፣ ተራግጠን ያደግን ፣ ጭቃ ስናቦካ
እንደዛሬው ሳይሆን ፣ ማንነቱን አውቆ ፣ በራሱ የሚመካ
ካገሩ ሲወጣ ፣ ከነጭ ሲቀላቀል ፣ ሲገባ አሜሪካ
ምን ነገር አገኘው ፣ አመመው መሰለኝ ፣ አይምሮው ተነካ
ይንተባተብ ገባ ፣ የራስ ቋንቋ ቀርቶ ፣ በፈረንጅ ሊተካ
ለካስ አብሮ አደጌን ፣ ያወቅኩት ሲመስለኝ ፣ አላውቀውም ለካ ።

ዜግነቱን ፍቆ ፣ የሌለ አገር ፈጥሮ ፣ እሱው ስሎ ካርታ
ክርክር ገጠመኝ ፣ ታሪክን አጣሞ ፣ ተሟግቶ ሊረታ
ያሁኑ ይባስ ሆነ ፣ ይግረምህ አለና ፣ ዘበናይ ጉደታ
ፊደልም አሳየኝ ፣ ቁቤ እሚባል ነገር ፣ የቫወል ጋጋታ
ሲያልቅ አያምር ሆነ ፣ ያብሮ አደጌ ነገር ፣ ይኸው ወደማታ
ያልሆነውን ሊሆን ፣ ያደፈርስ ጀመር ፣ ቁም ነገር ጨዋታ ።

ስልጡኑ ልጃቸው ፣ ታሪኩን የካደ ፣ ባባቱ አይመካ
ዛሬ ናላው ዞሮ ፣ ሚሲዮን በፃፈው ፣ የፈረንጅ ትረካ

**አገር ልናድ ይላል ፣ ጥላቻ እየከካ ፣ ጥላቻ እያቦካ ።**

**እራስን በመጥላት ፣ እራስን ማንኳሰስ ፣ እራስን ማዋረድ**
**የራስን አቃሎ ፣ እሩቅ አገር ሄዶ ፣ የባዕዱን መውደድ**
**አንድነት እያለ ፣ በጥላቻ መጓዝ ፣ ለመገንጠል መንጎድ**
**የተበተበውን ፣ ማን ይበጥስለት ፣ የጥላቻን ገመድ ።**

**ይህንን ያለዩት ፣ የወላጅ አባቱ ፣ ምንኛ ታደሉ**
**አምላክ ቢወዳቸው ፣ ባካላቸው ክፋይ ፣ ሳያሩ ሳይከስሉ**
**እጅን በጅ ሳይሉ ፣ ከእግዜር ሳይጣሉ ፣ ወልደው እንዳይገሉ**
**ቀድሞ ወሰዳቸው ፣ ሃጢያት እንዳይገቡ ፣ አንገቱን ሳይቀሉ ።**

**ታዛቢው ...** April 4, 2011

**“Those of you who sincerely believe that the unity and democracy of Ethiopia is not negotiable and paramount to the foundation of our struggle in bringing about fundamental change in Ethiopia, and yet confused by the proponents of AFD and COLABORATORS of OLF and ONLF and others anti Ethiopian Unity forces, please read again and again the OLF program and their vicious plan and unwavering agenda to dismantle the UNITY OF ETHIOPIA”.**

The Oromo Liberation Front (OLF) is a political organization established in 1973 by Oromo nationalists to lead the national liberation struggle of the Oromo people against the Abyssinian colonial rule. The emergence of the OLF was a culmination of a century old yearn of the Oromo people to have a strong and unified national organization to lead the struggle.

The fundamental objective of the Oromo liberation movement is to exercise the Oromo peoples' inalienable right to national self-determination to terminate a century of oppression and exploitation, and to form, where possible, a political union with other nations on the basis of equality, respect for mutual interests and the principle of voluntary associations.

The Oromo people's quest for their right to self-determination is just and legitimate. The aspiration of the people to regain their fundamental freedom is in line with the principle enshrined in the charter of the UNO. The OLF is struggling to enable the Oromo people to realize this fundamental right and bring an end to century old oppression. OLF's commitment to this objective is based on a democratic principle, that the Oromo people are endowed with the right to decide the type of sovereignty they want to live under and the type of political union they want to form with other peoples.

The change made by the Tigrean regime, that grabbed power from the Amhara rulers in 1991, is far from enabling the Oromo people and others to realize this fundamental right. It is merely a cosmetic change intended to affect the momentum of our just struggle. The OLF reiterates the struggle of the Oromo people is not directed against any people but the system of oppression. In fact the OLF and the Oromo people are committed to the noble cause of laying a foundation for union of free peoples on the basis of their freely expressed will. Source OLF

α **የኦነግንና የኦብነግን ሰንካላ አላማ በውክልና ሊያሳምኑን ለሚጥሩ ሁሉ ማሳሰቢያ !** Ω